;

# ክርስቶስ

በ G.C. 597

ሰዓት ካለፈ በህዋላ የሚመጣ የበረራ ትዕዛዝን አብዝቼ እጠለዋለሁ። ጥድፊያን ያስከትላል። ጥድፊያ ደግሞ ስህተትን ይፈጥራል። በረራ ላይ ስህተት መስራት ድግሞ ከማንኛውም የስራ መስክ ለየት ባለ ሁኔታ አስከፊ የሆነ አደጋን ያስከትላል። እየመሸ ሲሄድም ግዳጅ ለመወጣት ያስቸግራል።

አስመራ አየር ኃይል ምድብ ስር በሚገኘው የአርሚ አቪዬሽን ተርሚናል ቁጭ ብለን ካርታ እየተጫወትን ነበር። ከሰዓት በህዋላ ረፋዱ ላይ ስለነበር ከአንድ ተጠባባቂ ሄሊኮፕተር ክሩ (የአውሮፕላን ሰራተኞች) በስተቀር ቀሪ አባሎቻችን ለእራትና ለቢራ ወደ ክበብ አምርተዋል። ሜሎቲ ትልቁ ጠርሙስ ቢራ (ቅፅል ስሙ ኡጁሞ) ቀዝቅዞ እየጠበቀ ነው። ሳላስበው እራሴውኑ አስጎመጀሁና ምራቄን ዋጥኩ። ሰዓቴን ስመለከት አንድ ሰዓት ያህል ይቀረናል። ደርሷል እያልኩ ገና እራሴን ከማፅናናቴ፤ ስልክ ተደወለና ባስቸኳይ ወደ ናቅፋ በር መሄድ ያለበት ወታደር አለና እንደደረሰ በረራውን ቀጥሉ የሚል ትዕዛዝ ተላለፈ። መንገደኛውን አድርሶ ለመምጣት የቀረው ሰዓት ይበቃን ስለነበር ሄሊኮፕተሩን ለበረራ ስናዝጋጅ መንገደኛው ከተፍ አለ። በፖሊስ ታጅቧል። ለምን እንደሆን ስላልገባኝ የተርሚናሉን ፖሊስ አጣርቶ እንዲነግረኝ ላኩት። አጃቢዎቹም እንደው በደፈናው ለፍርድ ወደጦር ክፍሉ የሚላክ ወታድር መሆኑን ብቻ ከመግለፅ በላይ ሌላ ተጨማሪ መረጃ እንደሌላቸው አሳወቁን። በዚህ ሰዓት ለአንድ ወታደር ብቻ እንዴት ሄሊኮፕተር ይታዘዛል? ምን ያህል አስቸኳይ ቢሆን ነው? የሚሉት ጥያቄዎችን አዕምሮዬ እያሰላሰለ እረፍት ነሳኝ። የቀዝቃዛ ሜሎቲ ቢራው መስተጓጎልም ሊያነጫንጨኝ ከሚፈልጉት ምክንያቶች አንዱ መሆኑንም ልቦናዬ ይነግረኝ ነበር። አላስፈላጊ የሆኑ በረራዎች በስህተትም ሆነ ስህተትን መሸፈኛ ሆነው እንደሚከናወኑ የአደባባይ ሚስጥር ከሆነ ቆይቷል። ግንባር ላለ ጓደኛ፤ ለግል ለሆኑ ፍላጎቶች ማሟያ፤ለጥቅማጥቅም በጦርነት ሰበብ አውሮፕላኖችን ያላግባብ መጠቀሙ ካለ ሀፍረት ይሰራበታል። አቤት ብንልም የቁራ ጩኸት ሆኖ ቀርቷል። አለቆች ጆሮ ዳባ ልበስ ብለዋል። ሆነ ተብሎ የሚደረግ  ስህተት ለሰራዊቱ ውድቀት ቀዳሚ አመላካች ከሆኑት ምክንያቶች አንዱ ነበር። በዚህ ጽሁፍ ስለዚህ ጉዳይ መዘርዘሩ አመቺ ስላልሆነ ማለፉ ይሻላል።

የበረራ ቴክኒሽያኔን ከራሱ ከወታደሩ ሁኔታውን እንዲያጣራ ነገርኩትና የበረራ ዝግጅታችንን ቀጠልን። ከአስመራ ተነስተን ወደ ናቅፋ በር እንዳቀናን ቴክኒሽያናችን መንገደኛችን ከሆነው ወታደር ጠይቆ ያገኘውን እንደሚከተለው ተረከልን፦

ናቅፋ ግንባር ግዳጅ ላይ ካሉት ክፍለ ጦሮች የአንዱ አባል ነው። ከወር በፊት እሱና ሌላ አምስት ጓደኞቹን ፖለቲካዊና ወታደራዊ አሻጥር ሰርታችኋል በሚል ክስ ወታደራዊ ፍርድ ቤት ያቀርቧቸዋል። በፖለቲካውና በደህንነት ሃላፊዎቹ የተቋቋመ የይምሰል ፍርድ ቤት የሞት ቅጣት ይወስንባቸዋል። በተለይም በጦርነት ላይ ለሚደርስ ውድቀት ሰበብ ተፈልጎ የውድቀቱ ምክንያት እነ እከሌ ናቸው ተብሎ መረሸን እንደልማድ ከተያዘ ቆየት ብሏል። በመግደል የቀረውን የሠራዊት አባል በማስፈራራት ድል እንቀናጃለን የሚል የሞኝና የመሃይም አስተሳሰብ ይዘው የሚንቀሳቀሱበት ወቅት ነበር። እነኚህን ወታድሮች ፍርደ ገምድል ዳኛ የፈረደባቸውን የሞት ቅጣት እንዲፈፀምባቸው የራሳቸው የክፍል አባል የሆኑ ባልደረቦቻቸውን መርጠው ጊዝያዊ መቃብር አስቆፍረው ጉድጓድ ዳር በተርታ ያቆሙዋቸዋል። የአውቶማቲክ መሳሪያው ላንቃ ሲከፈት በጥይት የሚመቱት መውደቅ ይጀምራሉ። ዛሬ የያዝነውም መንገደኛ እራሱን ይስትና ይወድቃል። ጭለማ !

ምን ያህል ግዜ እንዳለፈ አያስታውስም ድንገት ይነቃል። ከላዩ ላይ የተጫነው ነገር ከብዶታል። ጭለማ ነው። ከሞት በህዋላ ወደ ገሃነም የወረደ ቢመሰለውም፤ እንደምንም ያለ የቀረ ኃይሉን ተጠቅሞ ላዩ ላይ ተጭኖት ያለውን ነገር ወደ ጎን አንፏቆ ከላዩ ላይ ሲያስወግድ ብርሃን

ታየው። እንደምንም እየተንገዳገደ ቆመ። አካባቢው ያለውን ጉድ ሲያይ ማመን ተሳነው። የጓደኞቹ እሬሳ ተጋድሟል። ግዚያዊው መቃብር በደም ተጨማልቋል። ከጉድጓዱ ዘሎ ወጣና ቆሞ ሰውነቱን በጥይት የተመታበት ቦታ ካለ ይፈትሽ ጀመር። ደግሞ ደጋግሞ ቢፈትሽም ምንም ነገር ሲያጣ መሬት ላይ ቁጭ ብሎ ማልቀስ ጀመረ። ሀዘንም ደስታም ተደበላለቀበት። የጓደኞቹን በጥይት የተደበደበ ሬሳ ሲያይ ምርር ብሎ ያለቅስና ለሀገር ደህንነት የህይወት መስዋዕትነት መክፈል ውለታው በእንደዚህ መከፈሉን ሲያሰላስል ንዴት ሰውነቱን ያንቀጠቅጠዋል። ሞትን በማይታመን ሁኔታ ማምለጡን ሲያስብ ደግሞ እግዚአብሄርን ማመስገኑን ይቀጥላል። ለብዙ ደቂቃዎች አለበት ቦታ ላይ ቁጭ ብሎ ቆየ። ድንገት አሁን ምንድነው ማድረግ ያለብኝ የሚለው ጥያቄ በአዕምሮው መጣበት። ወደ ገደለኝ ወገን መመለሱ የማይታሰብ ነው ብሎ ወሰነ። የነበረው ምርጫ ወደ ጠላት ወረዳ ማምራት ነበር። ጠላት እንደፈለገ ያድርገኝ ብሎ ወሰነ።

ቀኑ እየመሸ ነበር። የወገንና የጠላትን ይዞታ አካባቢው ባሉ ምልክቶች ለየና የሚሄድበትን አቅጣጫ ማጥናት ጀመረ። ምሽቱ ለዐይን መያዝ ሲጀምር ሙት ጓደኞቹን በእንባ ተሰናብቶ ወደ ጠላት ይዞታ ወደሆነው መሬት ጉዞውን ቀጠለ።ወደ 30 ደቂቃ እንደተጓዘ እንደ ብራቅ የሚጮህ ድምፅ ቀልቡን ይገፈዋል። እንደ ሀውልት ያለበት ቦታ ደርቆ ይቀራል። «ቁም» የሚል ድምፅ ነበር የሰማው። ሻዕቢያ እንዴት በአማርኛ ትዕዛዝ ይሰጣል? ወይንም እጁን ሊሰጥ የመጣ ወታደር ነው ብለው ይሆናል በአማርኛ የተናገሩኝ እያለ ሲያሰላስል፤«እንዳትነቃነቅ» የሚል ትዕዛዝ ተከተለ። ጭለማው በደንብ ስለማያሳይ ያስቆሙትን ሰዎች ለይቶ ማየት አቃተው። ትንሽ ቆይቶ የሰው ቅርፅ መለየት ቻለ። በረድፍ ሰብጠርጠር ብለው ወደሱ እያመሩ ነበር። አጠገቡ ሊደርሱ ትንሽ ሲቀራቸው ከመካከላቸው አንዱ « በስመ አብ! እከሌ አይደለም እንዴ ?» ብሎ ስሙን ጠርቶ ሲጮህ ወደ ጠላት ጎራ እሸሻለሁ ብሎ ወደ ወገን ጦር መመለሱን ሲያውቅ መሬት ላይ ወድቆ ተንሰቅስቆ ማልቀስ ጀመረ።

በማግስቱ ከሞት ስለተነሳው ወታደር ዜና ግንባር ያለው ጦር በአጠቃላይ ሰማው። ሁሉም ቀኑን ሙሉ የሚያወራው ርዕስ ሆኖ ዋለ። ቀን ረፋዱ ላይ ክርስቶስ የሚል ቅጽል ስም ወጣለት። ማታ ከተያዘበት ግዜ አንስቶ በጥበቃ ስር እንዲውል ተደረጎ አዛዡ፤የፖለቲካው ሃላፊና የደህንነት ሃላፊው ስብሰባ ተቀምጠው እንደገና ስለፈረደበት ምስኪን ወታደር ህይወት ዕጣ ፈንታ ለመወሰን ክርክር ገጠሙ። የጦሩ አዛዥ እንደገና የሞት ፍርድ መወሰን አግባብ እንዳልሆነ ገትረው ተከረከሩ። ሌሎቹ ነፃ ይለቀቅ ማለቱን ፈሩ። በመጨረሻም አስመራ ሄዶ የበላይ አካል ጉዳዩን እንዲያየው ተወሰኖ አስመራ ይላካል።አስመራ ያለው የበላይ አካል የራሳችሁን ችግር እራሳችሁ ፍቱ፤እኛን አይመለከትም ብሎ በሳምንቱ ወደ እናት ክፍሉ እንዲመለስ ያዛል። ለዚህም ነው ዛሬ ይዘነው ወደ ናቅፋ በር የምንበረው ብሎ ቴክኒሽያናችን ታሪኩን ቋጨልን።

« መከራው ያላለቀለት በሬ ከሞተ በኋላ ቆዳው ነጋሪት ይወጠራል » እንዲሉ የዚህም ወታድር ታሪክ የሰው ልጅ ምን ያህል መከራ ውስጥ ሊወድቅ እንደሚችል አመላካች ምሳሌ ነው ብዬ አሰብኩ። እኛ ያለንበትን የበረራ ካቢን ከመንገደኛ ክፍሉ የሚለየው በር ላይ ባለው መስኮት አጮልቄ ክርስቶስን ማየት ጀመርኩ። ተክዞ፤ ኩርምት ብሎ ተቀምጧል። እጅግ አድርጎ አሳዘነኝ። ከዛች የሞት ፍርድ ከተፈረደበት ዕለት ጀምሮ ምን ያህል ጭንቅና መከራ እንደተፈራረቁበት ለመገመት ያስቸግራል። ከፊቱ ላይ ስሜቱን ለማንበብ ብሞክርም ምንም አይነት ምልክት አጣሁ። ምናልባት ተስፋ መቁረጥና በሞት ጥላ ስር መመላለሱ ውስጡን ገድሎታል። ከአሁን በኋላ የሚንቀሳቀሰው በድኑ ነው እያልኩ ሳሰላስል መድረሻችንን ከሩቁ ታየንና ለማረፍ ዝግጅታችንን ጨርሰን ለማረፊያችን የምንጠቀምበት ሸለቆ ውስጥ ካለ ደረቅ ወንዝ ላይ ልናርፍ ስንል ድኝ ድኝ የሚል ሽታ አፈነን። ባትሪ ከመጠን በላይ ይሞቅና ሲፈላ የሚመጣ ሽታ እንደሆነ ስለምናውቅ ብዙም አላስደነገጠንም። አርፈን ባትሪዎቹን ስንፈትሽ ከስድስቱ ሁለቱ እንደማይሆን ሆነዋል። ሁለት ጤነኛ ባትሪ ያስፈልገናል። አስመራ ቴሌግራም ተደርጎ ለክፍላችን ተነግሮ በዕለቱ እርዳታ ማግኘት እማይታሰብ ነው። እየጨለመ እየሄደ ነው። መኪና ከክፍለ ጦሩ ጠቅላይ መምሪያ

አስመጣንና ወደዛው አቀናን። ክርስቶስም ከኛው ጋር ተጉዞ መምሪያው ስንደርስ ተሰናብቶን ወደ ክፍሉ አመራ። ለመጨረሻ ግዜ ይሆን የምናየው? ማን ያውቃል? እኛም መለዕክታችንን አስተላልፈን በነገው ዕለት በጠዋት ባትሪዎቹን ይዘውልን እንደሚመጡ አረጋግጠን ወደ ማረፊያችን አመራን። እየጨለመ ሄደ።

አንድ አነስተኛ ድንኳን ውስጥ ለሶስታችንም ቦታ ሰጡንና መሬት ላይ ቁጭ አልን። ከስር የሚነጠፍ ሸራና አንዳንድ ብርድልብስ ታደለን። ጃኬቴን አውልቄ ተንተራስቼው በጀርባዬ ተንጋለልኩ። የጓጓሁለት ቢራ ትዝ አለኝና ፈገግ አልኩ። ሁሌ ያሰቡበት እንደማይዋልና እንደማይታደር በተግባር ትምህርት ባገኝም ለምን ቶሎ ብዬ እንደምረሳው አይገባኝም። ከጓደኞቹ ጋር ስንጨዋወት እራት መጣልንና መመገብ ጀመርን። ኮሾሮና ኮምቦልቻ የሚታሸገው የቆርቆሮ ወጥ ሞቅ ተደርጎ ነበር ያቀረቡልን።«የምግብ ማጣፈጫው ረሃብ ነው እንደሚባለው» እጅ ያስቆረጥማል እያልን ጥርግ አድርገን በላን። ስንጨርስ ትኩስ ሻይ መጣልንና ጠጥተን እንደጨረስን በየቦታችን ጋደም አልን። እንቅልፍ ሊወስደኝ ሲል ክርስቶስ ትዝ አለኝ። እግዚአብሄር ካንተ ጋር ይሁን ብዬ አምላኬን ተማፅኜለት ተኛሁ።

እኩለ ሌሊት ገደማ ላይ የቀለጠ ተኩስ ከእንቅልፋችን ቀሰቀሰን። ተኩሱ ከቅርብም ከሩቅም ይሰማል። የነፍስ ወከፍ መሳሪያና ከባድ መሳሪያም ጭምር የሌሊቱን ፀጥታ አደበላለቀው። ስለሁኔታው ማን ይነግረናል እያልኩ ስጨነቅ ማታ እራት ያበላን ወታደር «ነቃታችሁል?» ብሎ ድንኳናችን ገባ። እስኪናገር በዝምታ ጠበቅነው። «ሻቢያ ጥቃት ጀምራ ነው፤ ይሄ አልፎ አልፎ የምትሞክረው ፍተሻ ስለሆን ብዙም አትስጉ። አስፈላጊ ሲሆን ተመልሼ እመጣለሁ» ብሎን ወጣ። «ምን ዓይነት አጋጣሚ ነው? ዛሬ ብናድር ዛሬ ጦርነት ይጀመር?» ብሎ ለብዙም ጉዳይ ደንታ የማይሰጠው ቴክኒሽያናችን የተለመደች የፌዝ ሳቁን አስከተለ። ረዳት ፓይለቴ ግን ጉዳዩ ለምን በፌዝ ይወሰዳል ብሎ ማማረር ጀመረ። እንግዲህ የመጣውን መቀበል ነው፤ሁኔታው በኛ ቁጥጥር ስር አይደለም ብዬ ገላገልኩና ሁልጊዜ እምሮዬን የሚከነክነኝ ጥያቄ ማሰላሰል ጀመርኩ።ወታደሩ የተናገረው ነው የቀሰቀሰብኝ። ለምን ጠላታችንን « አንቺ » እያልን በአንዕስታይ ፆታ እንደምንጠራ አይገባኝም። ጠላትን አንፍራው እንጂ ማክበር ግን ያስፈልጋል። አላስፈላጊ የሆነ ንቀት ለውድቀት ያዘጋጃል እንጂ እርባና እንዳልነበረው የሚታወቅ ሃቅ ነው። እንዲህ ያሉት ትንንሽ ስህተቶች ተደማምረው ወደ ቁልቁለት እየሰደዱን ነው እያልኩ ከራሴ ስሟገት ከኋላችን ሰማይና ምድሩን የሚደበላልቅ ድምፅ ቆሌያችንን ገፈፈው።ደማቅ የሆነ ብርሃንም አስፈሪውን ድምፅ እየተከተለ ሌሊቱን ቀን ያስመስለው ገባ።ከሶስት ደቂቃ በኋላ ተኩሱ ጋብ ማለት እንደጀመረ አስተናጋጃችን ወታደር ከተፍ አለ። «ቅድም ሳልነግራችሁ ቀርቼ ነው፤ ቢ፤ኤም መሣሪያ ያለው ከበስተጀርባችሁ ነው፤ እንዳትደነግጡ» ብሎ ፈትለክ ብሎ ወጣ። ምነው ሆዳችንን ሳንታመም ቅድም ብትነግረን እያልኩ ስለ ቢ፤ኤም መሳሪያ የማውቀው ትዝ አለኝ። መጀመሪያ ወደ ሃገራችን ገብቶ ያየሁት በደረግ ዘመነ መንግስት በኢትዮጵያና ሶማሊያ ጦርነት ግዜ ነበር።የኢትዮጵያ ጦር ለመሳሪያው አዲስ ስለነበረ መሳሪያው ለይ ተመድበው የሚሰሩት የመናውያን ባለሙያዎች ነበሩ። ቆሬ ጦር ግንባር ላይ የበረራ ድጋፍ ስንሰጥ ነበር ልተዋወቃቸው የቻልኩት። ባንደኛው ቀን የሎጅስቲክ ድጋፍ ሳደርስላቸው ምሳ ካልበላህ ብሎ አለቃቸው አጥብቆ ሲለምነኝ እሺ ብዬ ወደ ክልል ወረዳቸው ወሰደኝ። ምግባቸው ከሀገራቸው ስለሚላክላቸው ዓይነቱና መጣፈጡ ጦር ግንባር መሆኔን ያስረሳኝ ነበር። ምሳ ከበላን በኋላ ስለአዲሱ መሳሪያ ስጠይቀው እንደውም አዲስ ኢላማ ስላገኙ አሁን በጥቂት ደቂቃ ውስጥ ስለሚተኩሱ አይቼ እንድሄድ ጋበዘኝ። በደስታ ተቀብዬ ስጠባበቅ ካለምንም ማስጠንቀቂያ መሳሪያው ላንቃውን ከፈተ። ያለንበት መሬት ተንቀጠቀጠ። ብዙ ከባድ መሳሪያ አይቻለሁ እንደዚህ ድምፁ የሚያሸብር አልገጠመኝም። ወደ ሃያ የሚሆኑ ሮኬቶች በአንድ ግዜ ይተፋል። የየመኑ ጓዴ ሳቀብኝና ጀርባዬን ቸብ ቸብ እያደረገ ወደ መጣሁበት መልካም መንገድ ተመኝቶልኝ ሸኘኝ። ከምስራቁ ጦርነት በህዋላ አርባ የሚጎርሰው መጣ። ዛሬ ሌሊት ናቅፋ ግንባር ላይ የሚያጓራብን አዲሱ አርባ ጎራሽ ነበር።

ተኩሱ ፋታ አልሰጥ አለ።የነፍስ ወከፍ መሳሪያ እሳት ላይ እንደተጣደ ተልባ ይንጣጣል። አይ የእግረኛ ወታደር ኑሮ  ይሄኔ ስንቱ ወድቋል፤ ስንቱ ቆስሏል? እያልኩ ሳሰላስል ከጀርባችን ያለው ቢ፤ኤም እንደገና መሬቱን ያንቀጠቅጠው ገባ። ውጊያው ቀጠለ። ሊነጋጋ አካባቢ ተኩሱ ጋብ እያለ መሄድ ሲጀምር የተጨነቀው አእምሯችን ወደ እንቅልፍ አስተላለፈን። <ዶሮ ባይጮህም መንጋቱ አይቀርም> እንደሚባለው( ጦር ሜዳ ምን ያበደ ዶሮ ነው የሚኖረው? ) እንደማይነጋ የለም ነጋና ተነስተን አስተናጋችንን አስፈልገን አስጠራንና ወደ ሄሊኮፕተራችን የሚወስደን መኪና እንዲፈልግልን ተማጠንነው። ብዙም ሳይቆይ ዋዝ መኪና መጣልንና ተሳፍረን ቁልቁለቱን ነጎድን።

ሄሊኮፕተራችንጋ ደረስንና ከመኪናው እንደወረድን የያዘን ጭንቀት ቀለል አለልን። ሄሊኮፕተሩን በዐይኔ ስቃኝ ከስሩ የሆነ ሰው ተኝቷል። ምን ዐይነት ስርዐተ አልበኛ ወታድር ነው ብዬ ተጠጋሁና እየጮህኩ ከዕንቅልፉ ቀስቅሼ አስነሳሁት። አይኑን እየጠራረገ በደረቱ ተስቦ ከሄሊኮፕተሩ ስር ወጣና ቆመ። ዐይኔን ማመን ተሳነኝና ዐይኔን በተራዬ ጠራርጌ ደጋግሜ ማየት ጀመርኩ። ከፊቴ የቆመው ጉደኛው ክርስቶስ ነው። ጓደኞቼ በአንድ ላይ ክርስቶስ ብለው ጮሁ። «እንዴት ሆንክ?» ብዬ ጠየኩት። «ነፃ ወጣሁ ጌታዬ» ብሎ ሲመልስልኝ ሰውነቴን ደስታ ወረረውና ሳላውቀው ሂጄ ተጠምጥሜ አቀፍኩት። ጓደኞቼም መጡና ተረባረቡበት። በጦር ሜዳ ትዝታዬ ከተደሰትኩባቸው ገጠመኞች አንዱ ይሄ ነበር። ፋታ ስንሰጠው ታሪኩን እንዲህ ብሎ አወጋን፦

ከናንተ እንደተለየሁ ወደ ክፍሌ ሄጄ አመለከትኩ። መመለሴ አዲስ አልሆነባቸውም። ከአስመራ ተነግሯቸው ነበር። ስለኔ ጉዳይም ተወያይተውበት ውሳኔ ላይ እንደደረሱ አሳወቁኝ። በሰራሁት ወንጀል ግንባር ካለው ጦር ጋር መቆየት ስለማልችልና ወደፊት ጉዳዬ ተጠንቶ ውሳኔ እስኪሰጠው ድረስ ወደ አስመራ እንድመለስና ወደሌላ ክፍል እንድዛወር መወሰኑን አሳወቁኝ። የሰማሁትን ማመን ስላቃተኝ በህልሜ አለመሆኑን ለማረጋገጥ እራሴን መቆንጠጥ ነበረብኝ። እዛው ደርቄ ስቀርባቸው « ጨርሰናል » ብለው አሰናበቱኝ። ወዲያውኑ ወደ ሄሊኮፕተር ማረፊያ ሳይመሽብኝ ሩጫዬን ተያያዝኩት። ጠዋት ጥላችሁኝ እንዳትሄዱ ነበር ጭንቀቴ። ከመሸ ደረስኩና ዘቦቹን አስፈቅጄ እንቅልፍ እንኳን ቢወስደኝ ሞተር ስታስነሱ እንድሰማ ከስሯ ገብቼ ተኛሁ ብሎ አጫወተን።

ባትሪያችን በሄሊኮፕተር ደረሰልንና ገጥመን በሌሊቱ ውጊያ የቆሰሉ ወታደሮችን አግልለን አስመራ ገባን። እንደደረስንም ክርስቶስን የበረራ ቁርስ ጋብዘን በክፍላችን መኪና ፊያት 132 ከሃምሳ አለቃ ባዜ ጋር ወደ ቃኘው ላክነው። ስሰናበተው ብዙ ግዜ አብሮኝ የቆየ ጓደኛ የምሰናበተውን ያህል ነበር የተሰናበትኩት። እንባ ዐይኑ አቅርሮ ስለነበር የኔም ሳይመጣ ቶሎ ብዬ ተለየሁት። የሰው ልጅ ስንቴ ይሞታል የሚለው አረፍተ ነገር በአዕምሮዬ ለረጅም ግዜ እየተመላለሰ ክርስቶስን ያስታውሰኝ ነበር። ሌላው ሲገርመኝ የከረመው እውነተኛ ስሙን አለማወቄ ነበር።

የሃገራችን የርስ በርስ ጦርነት ከግዜ ወደ ግዜ እየባሰበት ይሄድ ነበር። ክርስቶስን ከተለየሁ ከሶስት አመት በኋላ ሲዳሞ ክፍለ ሃገር ለደቡብ ዕዝ ተመድቤ መስራት ጀመርኩ። አማፅያኑም እስከዚህ እንደ ሰሜኖቹ የተደራጁ ስላልነበሩ ውጊያው የጠነከረ አልነበረም። መንገድ የማይገባባቸው ቦታ ላይ ለሰፈረ ጦር የሚያስፈልገውን እርዳታ መስጠት ነበር ግዳጃችን። አሁን የቦታውን ስም ከማላስታውስበት ባሌና ሲዳሞ ድንበር ላይ ካለ ጥቅጥቅ ያለ ደን ውስጥ ግዳጅ ተሰጥቶን ሄድን። እንደደረስንም ሞተር አጥፍተን እግሬን ለማፍታታት የተፈጥሮውን ደን እያደነቅሁ ዞር ዞር ስል አንድ ወታደር ተከትሎኝ መጣና ትንሽ የሚቀመስና ጥሩ ብርዝ አለ ብሎ ግብዣውን አቀረበልኝ። ፈገግታው ብቻ እሺ ያሰኝ ነበር። እሺ ብዬ ግብዣውን ተቀብዬ አብሮኝ የሚበረውን ቴክኒሽያን አስጠርቼ ወደ አንድ ጎጆ ዘልቀን ገባን። አጎዛ የተነጠፈበት መደብ ላይ ቁጭ እንዳልን ወደጓዳ ገብቶ ትዕዛዝ ሰጥቶ ተመለሰ። እዚህ አካባቢ ያሉ ወታደሮች ለየት የሚሉት ጥቂቶች ሹሩባ ተሰርተዋል። እርግጥ ፀጉር ለመስተካከል የትኛውም ጦር ሜዳ እንደማያመች ቢታወቅም ነፈሬ ሲኮን ነው እንጂ ያየሁት ሹሩባ የሚሰራ ወታደር አጋጥሞኝ አያውቅም። እያስተናገደን ያለውም ወታደር ረጅም ሹሩባ ተሰርቷል። የወታደሮቹም ወዝ ፊታቸው ላይ ጨፍ ብሎ ይታያል። ኑሯቸው

የተሟላ እንደሆን ሰውነታቸው ይመሰክራል። ወታደሩ እጎኔ አስፈቅዶኝ ቁጭ ካለ በኋላ ጨዋታ ጀመረ። የባጥ የቋጡን እያወራን እያለን ወታደሩ ላይ የተለየ ሁኔታዎች አየሁ። ሳላየው እየሰረቀ ያየኛል፤ መለስ ብዬ ካየሁት አይኑን ይሰብራል። የሆነ የደስታ ስሜት አምቆ ይዟል። እየቆየ ከፈገግታው አልፎ ሳቁ እየፈነቀለው ይሄድ ጀመር። ብርዙ መጣልንና መጠጣት ጀመርን። « ይሄውሎት ጌታዬ የታደለው ጦር እንደዚህ ይኖራል፤ ያልታድለው ኮቾሮና የደፈረሰ ውሃ ይጠጣል» ሲለኝ እኔም እዚህ ያላችሁት የታደላችሁ ናችሁ ስል ምን የመሰለ የስጋ ጥብስ እየተንቻቻ ከጓዳ መጥቶ ቀረበ። ሌላ ወታደር የጣት ውሃ ይዞ ሲቀርብ ጎኔ ያለው ወታደር ማስታጠቢያውን ተቀብሎ « እሳቸውን የማስታጥብ እኔ ነኝ፤ ውለታ አለብኝ» ሲል እጄን ዘርግቼ የነበረውን ሰበሰብኩና «የምን ውለታ?» ብዬ ጠየኩት። ማስታጠቢያውን ቁጭ አደረገና « ጌታዬ ያስታውሱኝ ይሆናል ብዬ ብዙ ግዜ ሰጠህዎት፤ ሊያስታውሱኝ አልቻሉም፤ በርሶም አልፈርድም፤ ተለውጫለሁ። ሳልነግሮትም ይህንን ማዕድ መቁረስ የለብንም፤ ጌታዬ ክርስቶስን ያስታውሳሉ? » ብሎ ሲለኝ የማላውቀው ስሜት ሰውነቴን ወረረኝና አከላቴ ላይ ያለው ፀጉር ቆመ። ከሶስት አመት በፊት የመሰከርኩት አስደናቂ ታሪክ በለቤት እፊቴ ቆሞ ሳየው ምን እንደምል፤ ምን እንደማደርግ ግራ ገባኝ። የሱ ዐይን ቀድሞ ረጠበ። እኔም አለእፍረት ማልቀስ ጀመርኩ። እላዬ ላይ ተጠመጠመ። አብረውን የነበሩት ተደናግጠው ቆመው ቀሩ። ከጓዳ ምግብ ያዘጋጀችልን ሴት ብቅ ብላ በድንጋጤ <ምነው ምን ተፈጠረ?> እያለች ብትጠይቅ መልስ የሚሰጣት ጠፋ። ወደ ልቦናዬ ስማለስ ለቀቅሁትና « ውጭ ልውጣ ንፋስ ይምታኝ» ብዬ ከእቅፉ ወጥቼ ወደ በር ሳመራ እጄን ይዞ ተከትሎኝ ወጣ። «ሂድና ብሉ በላቸው» ብዬ መለስኩት። ወደ ውስጥ ሲገባ ዐይኔንና አፍንጫዬን መጠራረግ እንደጀመርኩ ተመልሶ መጣና አጠገቤ ቆመ። ምንም ሳንነጋገር ብዙ ቆየን። ምን መነጋገር ያስፈልጋል? አጋጣሚና ክፉ ግዜ ብዙ አሳይቶናል። ምግቡን እንብላ እንጂ አለኝ። አልበላም ይልቅስ ብርዙን አምጣልኝ ብዬ ውጭ ሆነን ብርዙን እየጠጣን ስለሶስት አመት ህይወቱ አጫወተኝ።

የመጣንበትን ጨርሰን ለመሄድ ስንነሳ ክርስቶስ በትልቅ ቅል ማር አዘጋጅቶ ስጦታ ሰጠኝ። አልተግደረደርኩም፤ ተቀበልኩት። ከዛ በህዋላ እንዳጋጣሚ ሆኖ አግኝቼው አላውቅም፤ በጓደኞቼ በኩል ግን የማር ስጦታው አልቀረብኝም። ከጥቂት አመት በህዋላ የሲዳሞው አመጽ መሪ ለመንግስት እጁን ሰጠና( ትዝ እንደሚለኝ አስተማሪ ነበር ) ሰላም ሲሆን ክርስቶስ የነበረበት የጦር ክፍል ወደ ሰሜን ጦር ግንባር መሄዱን ሰማሁ። ከዛ በህዋላ ተገናኝተን አናውቅም።

ሁለተኛውን ሞት እንደ መጀመሪያው አታሎ አልፎ ይሆን? ማን ያውቃል?